# ስለሺ ሙለታም ይፈታ!!

ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

ታየኝ አንባቢ " ደሞ እሱ ማነው? ስለሺ ሙለታ? " እያለ በመገረም ራሱን ሲጠይቅ። አወን ዛሬ በሃገራችን ሁላችንም የምናውቃቸው የፖለቲካ እስረኞች አሉ። እነዚህ መቶም ይሁኑ ሁለት መቶ በስም፤ በአድራሻ፤ በዝና፤ በፎቶግራፍ እኔም፤ አንባቢም፤ የአውሮዳ ፓርላሜንትም፤ የአሜሪካ ኮንግረስም፤ አምኒስቲ ኢንተርናሽናልም፤ ሂውማን ራይትስ ዎችም፤ ድረገፆችም....በተትረፈረፈ ማስረጃ የምናውቃቸው የአሸባሪው ስርአት ሰለባዎች ናቸው። ከአመት ተኩል ጀምሮ " በአስቸኳይ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ" እያልን በውሳኔም፤ በሰላማዊ ሰልፍም፤ በሻማ ማብራት ዘመቻም፤ በርሃብ አድማም ስንታገልላቸው ቆይተናል። ተፈቱ። እሰየው የሚያሰኝ ነው። ድሮውንም ቢሆን ህዝብ የሰጣቸው ቦታ ቤተ መንግስት እንጂ ወህኒ አልነበረም።

ስለሺ ሙለታስ? ስለሺ ሙለታን አንባቢ አያውቀውም። እኔም በወሬ ወሬ እንጂ አላውቀውም። ግን ደግሞ እስከዚህም "የወሬ ወሬ" ነገር ብቻ አይደለም። እርግጥ ስለሺ ሙለታ ጥቁር ይሁን ቀይ፤ ረዥም ይሁን አጭር፤ ቀጭን ይሁን ወፍራም በውል የማውቀው ነገር የለም። ነገር ግን እኔም ሆንኩ ሌሎች ዜጎች " መሪዎቻችን ይፈቱ " እያልን ስናካሂደው በቆየነው ትግል በግርጌ ማስታወሻነት መልክም ቢሆን "በሺህ የሚቆጠሩ" የፖለቲካ እስረኞች እያልን የምናወሳቸው ኢትዮጵያውያን አሉ። ስለሺ ሙለታ ከነዚህ የኢህአዴግ የግፍ አገዛዝ ሰለባ ከሆኑ ንፁህ ዜጎች አንዱ ነው። ከእስር ውጭ ያለው አለም በያዝ ለቀቅም ቢሆን "በአስቸኳይና ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ" እያለ ቢያወሳቸውም የነስለሺ መፈታት ጉዳይ እስከዚህም ቀላል ነገር አይደለም።

አንደኛ "ስለሺ ሙለታም ይፈታ!" ብለን ስንነሳ ይህ ራሱን የቻለ ሰፊ፣ ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ አጀንዳ እንደሆነና በዚህም የተነሳ ከፊታችን የሚጠብቀንን ትግል ከባድነትና ውስብስብ ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ሁለተኛ ደግሞ በነስለሺ ለእስር መዳረግ ምክንያት በየእለቱ የሚፈጠሩት ችግሮች ህብረተሰባችንን እንደ ድርና ማግ አስተሳስረው የያዙት የትግግዝና የመተሳሰብ እሴቶች ጨርሰው እንዳይወድሙ ከፈለግን "እስኪፈቱ ድረስስ?" የምትለዋን ለእነዚህ ወገኖቻችን የእለት ከእለት የህልውና ጉዳይና ለቀጣዩ ትግልም ለራሱ ደግሞ ወሳኝ የሆነችውን ጥያቄ አንስቶ በውል መመለስ ያስፈልጋል። ይህም "እስኪፈቱ ድረስ" የሚለው ጉዳይ ራሱን የቻለ ሰፊ የትግል አጀንዳ ነው። "ይፈቱ" የሚለው እልህ አስጨራሽ ሊሆን የሚችለው ትግል በአጠቃላይ ጨለምተኝነትና በህብረተሰባዊ ትጥቅ መፍታት ተውጦ የባሰውን የአቀበት ጉዞ እንዳይሆን ከፈለግን የትግል አጀንዳችን ሁለት በምንም ሊነጣጠሉ የማይችሉ ገፅታዎች ሊኖሩት ይገባል። እንዲፈቱ መታገል። እስኪፈቱ መታደግ።

## 1ኛ. እንዲፈቱ እየታገሉ እስኪፈቱ መታደግ

ከሞራል አንፃር ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ ትግልም እጅግ አሳሳቢ የሚመስለኝ ጉዳይ ሆኖ ሳለ እምብዛም ግን ዛቤ የሌለበት ጉዳይ ስለሆነ በሁለተኛው ነጥብ ልጀምር። "እስኪፈቱ መታደግ" የምለው ምን ለማለት ነው? የመጀመሪያውን የስለሺ ሙለታን ችግር በደርግም ሆነ በዚህ የወስላቶች ዴሞክራሲ ስርአት ስር በፖለቲካ እስረኛነት የማቀቀ ዜጋ ሁሉ የሚያውቀው ችግር ነው። ቀስ በቀስ ከእስር ውጭ ባለው አለም ከነመፈጠሩም የመረሳት ስሜት። ስለሺ ከታሰረ ሁለት አመት አልፎታል። ያኔ ሰሞኑ የተሟሟቀ የህዝባዊ ትግል ወቅት ነበር። ለስለሺ ሙለታ እስር ቤት ማለት ወርቅማ የትግል ጊዜ ከማባከን ሌላ ምንም ችግር አልነበረውም። ትልቁ ህልሙና ናፍቆቱ "መቼ ተለቅቄ ከዚህ ትግል ተደባልቄ" የሚል ብቻ ነበረ። ከታሰረ ወዲህ በወር ሶስት መቶ ብር ደመወዙ ቢቋረጥበትም ባለቤቱ የስንቅ ማቀበል ችግር አልነበረባትም። አራት ልጆቹም ቢሆኑ ዘመድ አዝማድና ጓደኛ ሌሎችም ከነመፈጠራቸውም የማያውቃቸው ዜጎች እየደረሱላቸው እስከዚህም የእለት ጉርስም ሆነ የትምህርት ቤት ችግር አልነበረባቸውም።

ትግሉም እየቀዘቀዘ፤ የእስር ዘመኑም እየተንዛዛ ሲሄድ በዙሪያው ሲተባበረው የነበረው ሁሉ መጀመሪያ
ላይ ነገሩን ሁሉ በያዝ ለቀቅ መያያዝ አመጣ። ቀስ በቀስ ደግሞ ትብብሩ ተቋረጠ። ይህ ከመሰላቸት ብቻ የመጣ ችግ
ር አይደለም። በቀጥታ ከሽብሩ የሚጠበቅና በአሸባሪዎቹ በኩል ደግሞ የሚፈለግ ውጤት ነው። በደርግም ዘመን አሸባ
ሪው አገዛዝ ንፁህ ዜጎችን ወህኒ ሲወረውር ገና ሳልታሰረው፤ ንፁህ ዜጎችን በጠራራ ፀሃይ ሲረሽን ደግሞ ገና ቆሞ ለሚ
ሄደው ዜጋ ሁሉ መልእክት የማስተላለፍ አላማ ነበረው። ''ይኸንን ያየህ ተቀጣ'' የሚል ቀጭንና ትጥቅ አስፈቺ መልእ
ክት። ዛሬም ቢሆን ሳናውቀውና ጨርሶ ልብ ሳንለው ይህ መልእክት ሙሉ በሙሉ ደርሶን ልክ አሸባሪዎቹ እንደሚመኙ
ት ህብረተሰባችን በአይናችን ስር እየፈራረሰ ነው። ዛሬ የስለሺ ሙለታ ቤት ተበትኗል። ሚስቱ ስንቅ ማቀበል ስላልቻ
ለች ለእለት ጉርሱ የሌሎች እስረኞችን ፊት ለማየት ተገዷል። ልጆቹ ምን በልተው እንደሚያድሩ አያውቅም። ትምህ
ርት እንዳቆሙ ሚስቱ ባትነግረውም በወሬ ወሬ ደርሶበታል። የስለሺ ሙለታና በሽህ የሚቆጠሩ የሱ መሰል ዜጎች ዋና
ው ሰቀቀን ዙሪያቸውን በሚስቶቻቸው፤ በባሎቻቸው፤ በልጆቻቸው ምናልባትም ጧሪ ባጡ ወላጆቻቸው ኪሳራ በመክ
ፈል ላይ ያሉት ይህ ከባድ መስዋእትነት ነው።

የዛሬ ሁለት አመት ''ለአገር ለወገን'' በሚል መንፈስ ተነሳስቶ ሲታገል ይህንን ተጋድሎውን ስለሺ ሙለ
ታ ብቻ ሳይሆን አካባቢውም ከጀግንነት እየቆጠረለት የመኩራራት ስሜት ነበረው። ዛሬ እየሰፈነ ባለው ጨለምተኝነት
የተነሳ ያ ሁሉ ጀግንነቱ ''ከሞኝነት'' ለመቆጠር ዳር ዳር እያለው ነው። ለሃገሬ ለወገኔ ሲል የነበረው ስለሺም ''ለማን
ብየ? ለምን ብየ?'' እያለ ራሱን መጠየቅ ጀምሯል። አካባቢውም የኢህአዴግ ማፍያ መልእክ-ት መቶ በመቶ ደርሶት ''እ
ኔም እንደ ስለሺ ሙለታ ልጆቼን የትም እንዳልበትን.....'' እያለ የትጥቅ መፍታት አዙሪት ውስጥ እየገባ ነው። አሸባሪዎ
ቹ ሌት ተቀን የሚያልሙት ህብረተሰቡ በዚህ መልክ እሴቶቹ ሁሉ ተፍረክርከው እንዲንበረከክላቸው ነበር። በተጨባ
ጭ ለነስለሸ ለመድረስ የመሞከሩና እንዳይሳካላቸው የመከላከሉ ጉዳይ የኛ የፖለቲካ፣ የሞራል፣ የሃገር፣ የወገን ሃላፊ
ነት ነው። ታዲያ ዛሬ ''በሽህ የሚቆጠሩ እስረኞች ይፈቱ'' እያለ በመታገል ላይ ካለው ዜጋ ማነው ለነስለሺ እይነቶቹ
ሰለባዎች ''እስኪፈቱ ድረስ'' ብሎ እየደረሰላቸው ያለው ሃይል። መራራው መልስ ማንም የለም የሚል ነው።

አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ይድረስላቸው ማለት የማይታሰብ ነው። ''አሉ፤ አቅሙም አላቸው!'' የሚባሉት የ
ሰብአዊ መብት ታሚጋች ድርጅቶች ለነስለሺ ሙለታ አይነቶቹ የፖለቲካ አፈና ሰለባዎች በተጨባጭ ለመድረስ የተበ
ጁ ድርጅቶች አይደሉም። ለምሳሌ አምኒስቲ ኢንተርናሽናልን ወስደን ተልእኮውንና ተግባራቱን በዝርዝር የሚያቀርቡ
ዶኩሜንቶችን ስንመለከት የዚህ ድርጅት አባላት ''በግለሰብ ደረጃም ሆነ በቡድን'' ተሰማርተው የሚሰሩት በሰባት ዋና
ዋና አቅጣጫዎች ሆኖ እናገኘዋለን። እነዚህም 1ኛ. ከፖለቲካ እስረኛው ጋር መፃፃፍ 2ኛ. ከፖለቲካ እስረኛው ቤተሰቦ
ች ጋር መፃፃፍ 3ኛ. ለፖለቲካ እስረኛው ቤተሰቦች የገንዘብና ሌላ ማቴርያል እርዳታ መስጠት 4ኛ. ለፖለቲካ እስረኛው
የገንዘብና ሌላ ማቴርያል እርዳታ ማድረግ 5ኛ. ስለፖለቲካ እስረኛው ሁኔታ ተቃውሞ ማሰማት 6ኛ. የፖለቲካ እስረኛ
ው ጉዳይ በፍርድ ሲታይ የጠበቃ ወጭውን መሸፈን 7ኛ. ስለ ፖለቲካ እስረኛው ሰፊ የሆነ መረጃ ማሰራጨት የሚሉ ና
ቸው።

የፅሁፌ ዋና መልእክት እንደ ስለሺ ሙለታ ላሉት በሽህ ለሚቆጠሩ ዜጎች ''የህልውና ችግር'' የመድረስ
ነገር ከተነሳ ''አለም አቀፍ ኮሙኒቲውን መርሳት ያስፈልጋል'' የሚል ነው። ስለሆነም ከነዚህ ተግባራት ውስጥ ስንቱ
ናቸው ለነሱ የሚሰሩት የሚለውን ጥያቄ ዝርዝር ውስጥ አልገባም። እዚህ ላይ የሚመለከቱን ለእስረኛውና ለቤተሰቦቹ
የማቴርያል-ና የገንዘብ እርዳታን የሚያወሱት ነጥብ ሶስትና አራት ናቸው። ይህ ነጥብ እነስለሺን ይመለከታል ወይ? መ
ልሱ አጭር ነው። በአምኒስቲ ኢንተርናሽናል ማንዴት መሰረት እነስለሺ ሙለታም ልጆቹም፤ ባለቤቱም፤ ወላጆቹም ለ
ተጨባጭ እርዳታ አይበቁም ወይም ''ኳሊፋይ'' አያደርጉም። ለምን?

የአምኒስቲ ኢንተርናሽናል የአሰራር መሰረታዊ መርህዎች አራት ናቸው። እነሱም 1ኛ. ፍፁም ህጋዊነት 2
ኛ. ፍፁም ገለልተኛነት 3ኛ. አለም አቀፋዊነትና 4ኛ. የሚሰጠው ድጋፍ በግለሰቡ ላይ ማተኮር ወይም (ፔርሶናላይዜሽን
ኦፍ አክሽን) የሚሉት ናቸው።. እኛን እዚህ የሚመለከተን ጥያቄ አራተኛው ነው። ከፍ ብለን የዘረዘርናቸው የአምኒስቲ
ተልእኮዎች (ምናልባት 'ተቃውሞ ማሰማት' ከሚለው ሌላ) የሚሰሩት በደፈናው ''ለፖለቲካ እስረኞች ሁሉ'' አይደለ

ም። አምነስቲ ኢንተርናሽናል አለኝ የሚለው ተልእኮ "*በውል ማንነታቸው የታወቀ፤ በስም እገሌ የሚባሉ፤ በዚህ ሙያ
ተሰማርተው የነበሩ፤ የት እንደሆነ በሚታወቅ እስር ቤት በዚህ ሁኔታ የሚገኙ፤ እገሌ የተባለ ባለስልጣን በፈፀመው ህገ
ወጥ እርምጃና በዚህ በዚህ ሁኔታ የታሰሩ ዜጎችን ከእስር ለማስፈታት*" የሚል ነው። በመሆኑም የእነዚህን በማንነታ
ቸውና በተያዙበት እስር ቤት የሚታወቁ እስረኞች ጉዳይ እንደ አግባቡ ለተወሰኑ ግለሰቦችም ሆነ ቡድኖች በባለቤትነት
እየሰጠ የሚታገል ድርጅት ነው።

ችግሩ እንግዲህ አምኒስቲም ራሱም ይገነዘበዋል። እንዲህ አይነቱ አሰራር አፈናን ከሌሎች በርካታ የአገ
ዛዝ ስልታቸው እንደ አንድ ተቀጢላ መሳሪያ አድርገው በሚወስዱ "መደበኛ" አፋኝ አገዛዞች ስር ሊሰራ ይችላል። የ
አገዛዙ የህልውና መተማመኛ እናቱም አባቱም አጠቃላይ ሽብር በሆነበትና ሌላ ምንም ባልቀረው ስርአት ስር ግን አይሰ
ራም። በዚህ ስድ ስርአት በዜጎች ላይ የሞት ሽረችና የማሰር የመፍታት "መብት" ያላቸው ባለስልጣናት ቁጥር ከመበ
ርከቱ የተነሳ ሌላው ቀርቶ ራሳቸው የሃገሪቱ መሪዎች ስለታሰሩት ሰዎች ስምና አድራሻ ቀርቶ በአንድ በተወሰነ ወቅት
በሃገሪቱ ምን ያህል የፖለቲካ እስረኞች እንዳሉ እንኳን የማያውቁበት ሁኔታ እንዳለ ይናገራል። በደርግ ዘመን በተደጋ
ጋሚ በሚወጡት ሪፖርቶች አምኒስቲ "በግምት" በሃገሪቱ ሰላሳ ሽህ ያህል የፖለቲካ እስረኞች እንዳሉ ይናገርና እዛው
በዛው ደግሞ " አምኒስቲ ኢንተርናሽናል በምስጢር ሰብስቦ በያዘው ሊስት ውስጥ የተመዘገቡት እስረኞች ቁጥር አራ
ት መቶ እንኳን አይሞላም!!" ይል ነበር። የማቴርያል እርዳታ ቢኖር እንኳን በነዚህ አራት መቶ የማይሞሉ ዜጎችና ቤ
ተሰቦቻቸው ብቻ የተወሰነ ነበር ማለት ነው።

ኢትዮጵያውያን ወገኖቹስ? የሃገራችን ዴሞክራቶች በአጠቃላይና በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ በተለይ የሚ
ታገሉ ድርጅቶች ዋናው አላማ በሃገራችን የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ መታገል ነው። ይህ ትክክለኛና የተቀ
ደሰ ተጋድሎ በመሆኑ ተፋፍሞ መቀጠል እንዳለበት የሚያጠራጥር አይደለም። ጥያቄው ግን እዚህ ላይ ብቻ አይደለም
። ታግለን፤ ገና "ዘንቦ ተባርቆ" ዴሞክራሲ አሰፍነን፤ እናስፈታችኋለን ለሚለው አነጋገራችን እነ ስለሺ ሙለታ "እኔ እ
ምሞተው ዛሬ ማታ! እሸት የሚደርሰው ለፍልሰታ!" በሚል መንፈስ "እስከዚያስ?" የምትል አጭር ጥያቄ ያቀርቡልናል
።

ከዚህ አንፃር ሲታይ የኛ የኢትዮጵያውያን አካሄድ ከፈረንጆቹ እምብዛም አይለይም። ከላይ እንዳልኩት
እነ ስለሺ ሙለታ እንዲፈቱ ስንታገል "እስኪፈቱ" ድረስ ህብረተሰባችንን ድርና ማግ ሆነው አያይዘው እንደ ህብረተ
ሰብ አስተሳስረውት የቆዩት የትግግዝ፤ የመተሳሰብ፤ የሃገር ወገን ስሜት እሴቶች በየእለቱ ትንሽ ትንሽ በመበጣጠስና በ
መፈራረስ ላይ ናቸው። እነዚህ እሴቶች እየሰፈነ ካለው ግራ መጋባትና ጨለምተኝነት ጋር "ከራስ በላይ ንፋስ" በሚለ
ው ክፉ አባዜ እየተተኩ መሆናቸውን ተገንዝበን ለዚህ አሳሳቢና ትጥቅ አስፈቺ ጉዳይ መፍትሄ ስናቀርብ አንታይም። የ
ትጥቅ ትግል አካሂዳለሁ ብሎ የሚነሳ ሃይል በየግጥሚያው ጉዳት ለሚደርስባቸው ቁስለኞች ለመድረስ አስፈላጊውን
ዝግጅት ሳያደርግ በዚህ የትግል መስክ መሰማራቱ የማይታሰብ ነው። እርግጥ የነስለሺም የኛም ተጋድሎ ህጋዊ፣ ህዝባ
ዊና ሰላማዊ ተጋድሎ እንጂ የትጥቅ ትግል አይደለም። ይህም ሆኖ ከትጥቅ ትግል ባላነሰ ጀግንነትን የሚጠይቀው ህዝ
ባዊ ትግላችን ከትጥቅ ትግል ባላነሰም "ቁስለኞችን" የሚፈለፍል ተጋድሎ ነው። እንደ ስለሺ ሙለታ በሰላማዊው ትግ
ል መስክ የቆሰሉ ዜጎች በሽህ የሚቆጠሩ መሆናቸውን ሁላችንም እናውቃለን።

ለምን አንደርስላቸውም? ችግሩ በተለይ ዛሬ ዲያስፖራው ባለበት ከሞላ ጎደል የተመቻቸ ሁኔታ የገንዘብ
ም የማቴርያልም ችግር አይደለም። የስለሺ ሙለታ ኑሮ የተናጋው በወር ሶስት መቶ ብር ደመወዙ በመቋረጧ ነው። ሰ
ላሳ ዶላር አትሞላም። ይች ብትገኝ ለሱም ስንቅ አቀብለን፤ ልጆቹም ጠግበው እንዲያድሩና ትምህርታቸውንም እንዲ
ቀጥሉ እናደርጋለን። ይህንን ስናደርግ ደግሞ ጥቅሙ የማቴርያል ጥቅም ብቻ አይደለም። የኢህአዴግ መሪዎች ከጦር
የሚፈሩት የትግግዝ መንፈስ በህብረተሰባችን እንደገና እንዲያንሰራራ አደረግን፤ የትግል ሞራል እንዳይወድቅ እንከላከ
ላለን። ይህንን ካደረግን ደግሞ በአሸባሪዎቹ ላይ የማይናቅ የፖለቲካ፤ የስነ ልቡናና የሞራል ድል ተጎናፀፍን ማለት ነ
ው። ያኔ ህዝባችንን "ተነስ! ታገል!" ብንለው እኛም ያምርብናል። ህዝባችንም ያዳምጠናል።

ችግሩ የገንዘብ ሳይሆን የግንዛቤ፤ የአሰራርና የአደረጃጀት ብቃት ችግር ብቻ ነው። በሽህ ለሚቆጠሩ ሰለ
ባዎች በዚህ መልክ ለመድረስ መሞከር በጣም ውስብስብ ስራ እንደሆነ አይካድም። ግን ድሮም ቢሆን የተያያዝነው ት

ግል ቀላል ነው ያለ ማንም የለም። ለዚህ ነው ትግላችን ከተራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ትግል አልፎ ዘርፈ ብዙና ሁሉን አቀፍ መሆን ይኖርበታል የሚባለው። ለዚህ ነው ከዚህ ውስብስብ ትግል በድል አድራጊነት ለመውጣት ከተፈለገ ኢዴ ሃህ በጠራው መልክ አንድ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ መጠራት ያለበትና በዚህ ጉባኤ ላይ ይህ የትግግዝ አጀንዳ እንደ ዋና ጉ ዳይ ተቆጥሮ የሰብአዊ መብት ተሟጋች የሆኑ ኢትዮጵያዊ ስብስቦችም ሆኑ ሌሎች ዜጎች በሽህ ለሚቆጠሩት የሰላማዊ ው ትግል ቁስለኞች ለመድረስ አንድ ስትራቴጂ መንደፍ የሚያስፈልገው።

ሁለተኛው ጥያቄ " ስለሺ ሙለታም ይፈታ!" በሚል መፈክር ስር የምናካሂደውን የትግል መስክ ይመለ ከታል። የዚህ ሰፊ አጀንዳ ቀላሉና የመጀመሪያ መጀመሪያ ትርጉም በግንቦትም ሳቢያ ሆነ ከዚያ በፊት ታስረው የሚገ ኙ ወገኖቻችን በሙሉ ከእስር ተፈትተው ኢትዮጵያችን የፖለቲካ እስረኛ አልባ የሆነች አገር ትሁን ማለት ነው። ግን ደግሞ ይህ ብቻ አይደለም። እነ ስለሺ ይፈቱ ማለት ከእንግዲህ ማንም ዜጋ በመአከላዊ መንግስትም ደረጃ ሆነ በጋጠ ወጥ የመንደር ካድሬዎች የዘፈቀደና የእብሪት ውሳኔ ጥጃ ይመስል ነጋ ጠባ መታሰር መፈታት የሚሉ ግፍ እንዳይፈፀ ምበት መታገል ማለት ነው። እነ ስለሺ ሙለታ ይፈቱ ብሎ መታገል ማለት በህብረተሰባችን ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ የ ህግ የበላይነት እንዲኖር፣ የዳኝነት ነፃነት እንዲረጋገጥ፣ ተጠያቂነትና ግልፅነት እንዲኖር መታገል ማለት ነው። ህብረ ታችንም ሆነ ቅንጅት በዚህ ጉዳይ በጣም ግልፅ የሆኑ ሃገራዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ አቋሞችና አጀንዳዎች ይዘው ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል።

ትግላችን ዴሞክራሲ የሰፈነበት፤ ብሄራዊ እርቅና ሰላም የወረደበት የተረጋጋ ህብረተሰብ ፈጥረን ፍትሃዊ ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት የሚደረግ ታሪካዊ ተጋድሎ ነው። ኢዴሃህ ለምርጫ ውድድር ሲገባ ይ ፋ ባደረገው አማራጭ ሰነድ ለነዚህ ለዴሞክራሲ ግንባታና ከሱ በምንም አይነት ተነጥሎ ለማይታየው ሃቀኛ ብሄራዊ እ ርቅ አጀንዳ ከፍተኛ ቦታ ሰጥቷቸዋል። ለዚህም እውነነት ደግሞ በዴሞክራሲያዊው የሽግግር ወቅት አንድ የዴሞክራ ታይዜሽን ኮሚሽንና ሌላ ደግሞ የኢህአዴግ አባላትን ጨምሮ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ተቋማት ተወካዮች፣ የሃ ይማኖት መሪዎች፣ የሃገር ሽማግሎች፣ ምሁራን .... ....የሚሳተፉበት የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽን እንዲቋቋም ሃሳብ አቅር ቧል።

የቅንጅት መሪዎችም ሆኑ ሌሎች በሽህ የሚቆጠሩ ዜጎች ለግፍ እስር የተዳረጉት እንዲሁም በመቶ የሚ ቆጠሩ ንፁሃን በጠራራ ፀሃይ የተረሸኑት ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን እሴቶች የሚያጠቃልሉትን የግንቦት ድሎችን የማስ ከበር አላማዎች አንግበው ያካሄዱት ህጋዊ ትግል እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው እንደሆነ እናውቃለን። በዚህ መነሾ ለ ግፍ እስር ከተዳረጉት መሃከል ዛሬ ጥቂት ወገኖቻችን ተፈቱ። ከላይ እንዳልኩት እሰየው የሚያሰኝ ነው። ከእንግዲህ ስ? የሚለውን ጥያቄ በቅጡ ለመመለስ በእነዚህ ወገኖቻችን መፈታት ከሚሰማን ደስታና ዘልቀን ድሮውንም ቢሆን የጠ ቡ መነሻ ከሆኑት የግንቦት ድሎች፣ የብሄራዊ እርቅና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች አንፃር የት ደርሰናል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሞከር ያስፈልጋል።

## 2ኛ. ብሄራዊ እርቅ፣ዴሞክራሲ ግንባታ - የት ደርሰናል?

ለዚህ ጥያቄ መልሱ ቢያንስ ለኔ በጣም ግልፅ ነው። በወገኖቻችን መፈታት ማግስት ከላይ አላማችን ብለ ን ከዘረዘርናቸው እሴቶች አንፃር በአንድኛቸውም የወደፊት እርምጃ የለም። እነስለሺ ሙለታ ይፈቱ በሚለው አጀንዳ ዙሪያ የሚካሄደው ሰፊ ትግል ገና ከፊታችን እንደሆነ በምንም በማያሻማ መልክ መቀመጥ ይኖርበታል። በአይናችን ስር እየተከሰተ ያለውን ሁኔታ በጥሞና ስንመለከት ዛሬና በመጭዎቹ ወራት በቅድመ ግንቦት ቀርቶ በግንቦት ማግስት ወ ገኖቻችን ከመታሰራቸው በፊት በነበሩት ሳምንታትና ወራት ወደ ነበረው የዴሞክራሲ ፍንጭ ሁኔታ እንኳን እንዳልተ መለስን በግልፅ እናያለን። ያለንበት ሁኔታ ፈረንጆቹ እንደሚሉት "ባክ ቱ ስክዌር ዋን" ወይም ደግሞ "ከርሞ ጥጃ" የ ሚባል አይነት እንኳን አይደለም። "አንስ ሲሉት ተቀንስ" የተባለው አይነት ሁኔታ ውስጥ እንደምንገኝ መገንዘብ የግድ ነው። ከዚህም አልፎ መሄድ ይቻላል። ያለንበት ሁኔታ በብሄራዊ እርቅ ስም በሃቀኛ ብሄራዊ እርቅ ጎዳና ላይ እንቅፋ ት የተደነቀረበት፣ በዴሞክራሲ ሂደትና ግንባታ ስም ለዚህ አላማ ወሳኝ በሆነው በህዝባችን የትግል ተሳትፎ ላይ ህገ ወ

ጥ የሆነ ተአቅቦ የተጣለበት ሁኔታ ነው። ይህንን ሃቅ መገንዘብ ካልቻልንና የቀጣይ ትግል ስትራቴጂያችንን ከዚህ አፍ
ጦና አግጦ ከፊታችን ከተደቀነው እውነታ ተነስተን ለመቀየስ ካልተነሳን በመጭው ጊዜ ውጥንቅጡ ለወጣ ውዥንብር
በሩ ተበርግዶ ተከፍቶ የሃገራችን ሰላም፣ አንድነትና ዴሞክራሲ ባለቤት ያጡ አጀንዳዎች ሲሆኑ እንደሚችሉ በግልፅ
ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

ነገሩ እንደዚህ ሆኖ ሳለ ሰሞኑን ጆሯችን እስኪደነቁር ድረስ በወያኔ/ኢህአዴግ ደጋፊዎችና ይህንን ሁኔታ
ባስቻሉት ሸማግሌዎችም ሆነ በአንዳንድ ግልብ የፈረንጅ "ተንታኞች" አካባቢ የሚዘፈንብን ከዚህ ጨርሶ የተለየ ሙዚ
ቃ ነው። እንደነዚህ ወገኖች አባባል በቅንጅት መሪዎች መፈታት ሳቢያ የግንቦት ማግስቱ ቀውስ የመፍትሄ ጅማሮ አያ
ገኘ ነው፣ መስመር የሳተውና የተቀለበሰው የዴሞክራሲ ሂደት መልሶ በእግሩ እየቆመ ነው፣ በሃገራችን የብሄራዊ እርቅ
ሂደት በጎ ጅማሮ ተከስቷል፣ ቀጣይ ችግሮች ቢኖሩም እነሱም በድርድር፣ "በሃገር ባህል" እሴቶቻችንና በሽምግልና
ሊፈቱ ይችላሉ.......እየተባለ ነው። የተያዘው ሂደት የብሄራዊ እርቅም የዴሞክራሲ ግንባታም በጎ ጅማሮ ሳይሆን እንዲ
ያውም የነዚህ ተፃራሪ ነው።

### ሀ/ "የብሄራዊ እርቅ በጎ ጅማሮ" እንዳንባል።

በኔ ግምት እነዚህ ወገኖቻችን የተፈቱበት ሁኔታ በጥልቀት ቀርቶ ላይ ላዩን እንኳን ሲታይ የተያዘው የብ
ሄራዊ እርቅ ጉዞ አይደለም። ህብረተሰባችን "ብሄራዊ እርቅ እንዲህ ከሆነ በአፍንጫችን ይውጣ" ሊል የሚችልበት አ
ደገኛና ጭራሹን ይህንን ሁላችንም የምንመኘውን በጎ ሂደት የሚያደናቅፍ አካሄድ ነው።

መጀመሪያ ነገር "ብሄራዊ እርቅ" ሲባል ማን ከማን ተጣልቶ ማን ከማን እንደሚታረቅ ግልፅ መሆን አለ
በት። እርቅ ማን ከማን? የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ጠባቸው ለእስር ከተዳረጉት ጥቂት የቅንጅት መሪዎች ጋር ብቻ አ
ይደለም። ድምፃቸው ከተዘረፈው፤ መብታችን ብለው በታገሉ በጠራራ ፀሃይ ከተረሸኑት ዜጎች ወዳጆች፣ ወላጆች፣ ዘ
መድ አዝማድና የትግል አጋሮች፣ በደርዘን ሽህ እየተቀጠሩ ለእስር፣ ለእንግልትና ለስደት ከተዳረጉ ዜጎች፣ ከጨካኝ
የመንደር ካድሬዎች አይን ለመሰወር ከቀያቸው ርቀውና ከቤተሰብ ተፈናቅለው ስውር ኑሮ ለመምራት ከተገደዱና በአ
ጠቃላይ ለተሻለ ቀን፣ ለተሻለ ኑሮ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሰላም፣ ለሃገር አንድነት በመቆም "ድምፄ ይከበር" ብሎ ከተነሳ
ው ከመላው ህብረተሰባችን ጋር ነው። ለዚህ ነው እርቅ ሲባል እገሌ ከእገሌ ወይም ደግሞ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪ
ዎች ከመንግስት ጋር የሚታረቁበት ጠባብ ሂደት ሳይሆን ከዚህ የሰፋ "ብሄራዊ" ይዘት እንዲኖረው የሚያስፈልገው።

ሁለተኛ እርቁ "ብሄራዊ" እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ "የብሄራዊ ግጭቱ" መሰረታዊ ምክንያት በግልፅ ተ
ቀምጦ ለሱ መፍትሄ መፈለግ ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር ሲታይ አንድ ምክንያት ቢሆንም የነዚህ ወገኖቻችን ለእስር
መዳረግ የግጭቱ ዋናው መነሾ እንዳይደለ ግልፅ ነው። የግጭቱ መሰረታዊ ምክንያት ሚሊዮኖች በትግልና በመስዋእት
ነት ያገኟቸው የግንቦት ድሎች መነጠቃቸውና የዴሞክራሲ ግንባታው ሂደት መቀልበሱ አንሶ በሃገራችን ከግንቦት በ
ፊት የነበረችው የዴሞክራሲ ፍንጭ እንኳን በአመፅ ተደምስሳ ጨርሶ ደብዛዋ የጠፋበት እጅግ አደገኛ ሁኔታ በመፈጠ
ሩ ነው። በመሆኑም እርቅ የሚሉ ነገር የጠቡን መነሾ ምክንያቶች ማለትም የዴሞክራሲን ጉዳይ በአንድ አፍታ መፍታ
ት እንኳን ባይችል ለዚህ መንገዱን የሚያመቻች ሂደት መሆን ይኖርበታል ማለት ነው።

ሶስተኛው ችግር እዚህ ላይ ነው። ይህ እርቅ "ውሸልሸል" እንዳይሆን ከተፈለገ እነዚሁ የግጭት መነሾ
ዎች ነገ ለሌላ ግጭት በር እንዳይከፍቱ በሰላም ሊፈቱ የሚችሉበት የእርቅ መዳብሪያ መንገድ ወይም ሜካኒዝም ያበጀ
ሂደት መሆን ይኖርበታል። የሽማግሌዎቹ "የብሄራዊ እርቅ" ሂደት በቀጣዩ ጊዜ እርቅ የሚያዳብር ሳይሆን አልፎ ተርፎ
ም የሃቀኛ ብሃራዊ እርቅ ጎዳናን የሚዘጋ አጉል አካሄድ ነው። ኢዴፓህ በተደጋጋሚና በትክክል እንዳስቀመጠው ትርጉ
ም ያለው "ብሄራዊ እርቅ" በምንም አይነት ከህዝባዊ ድልና ከዴሞክራሲ ቀድሞ ሊሰፍን የሚችል ነገር አይደለም። ለ
ወገኖቻችን መፈታት በር የከፈተው የእርቅ ተብየ ሂደት ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ ከምኑም የለበት ማለት ይቻላል። ለ
ዛውም እንግዲህ ሌላ ቁም ነገር አለ። "ብሄራዊነቱ" ቀርቶ እጅግ ጠባብ በሆነ መልኩ ሲታይ እንኳን ይህ "የእርቅ" ተ
ብየ ሂደት ከዘላቂው የብሄራዊ እርቅ አላማችን አንፃር ሁለት አይነ የሚያወጡ ጉድለቶች አሉት።

መጀመሪያ ነገር ለነዚህ ወገኖቻችን መፈታት በር የከፈተው ሽምግልና "በሃገር ባህል መሰረት የተካሄደ" የሚሉ አነጋገር ጨርሶ ቦታ እንደሌለው በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል። "ብሄራዊነቱን" ለጊዜው ወደ ጎን ትተንና የእ ርቁን ሂደት በተፈቱት ወገኖቻችንና በወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ወስነንና አጥብበን ስናየው የምንገነዘበው ምንድን ነው? ሂደቱ የሃገር እጣ ፈንታ ጉዳይ ቀርቶ "በሃገራችን ባህል መሰረት" የባልና ሚስት ጠብ ከመሸምገል ሂደት ጋር እንኳ ን የሚመጥን አይደለም። በሃገራችን ባህል "ሽምግልና" ሲባል ሁለቱ የሚታረቁ ወገኖች ወይ የየበኩላቸውን ጥፋቶች አምነው ተቀብለው "አንተም ተው አንተም ተው" ተባብለው ይቅርታ ሲደራረጉ፣ ወይ ደግሞ የበደለው ወገን ይቅርታ ጠይቆ፣ የተበደለው ወገን ደግሞ ሽማግሎቹንም ህብረተሰቡንም አክብሮ ይቅር ብሎ እርቅ የሚወርድበት ሂደት ነው። ይኸኛው የእርቅ ተብየ ሂደት የተገላቢጦሽ ተበዳዩ በዳዩን ይቅርታ ለመጠየቅ የተገደደበት እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነ ው። እነ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ "በሃገራችን ባህል" የሚሉት ነገር የግድ ከባህላችን ጋር ግንኙነት ይገኝለት ከተባለ አካሄዳቸው የሚገናኘው እክ እንትፍ ብለን ልናስወግደው ከሚገባን "ማን በደለ ወታደር ማን ይካስ ባላገር" ከሚለው "ባህል" ጋር ነው። በመሆኑም ህዝባችን ለወደፊቱም "ሽምግልና" በሚሉ ነገር ተስፋ እንዳይቆርጥ ከፈለግን ፕሮፌሰሩ ን ወይ "በቃዎት!" ወይ ደግሞ ጥረትዎን በእርግጥ በአስከፊው ሳይሆን በበጎ "ባህላችን" መሰረት አስተካክለው ለእውነ ተኛ እርቅ ይስሩ ማለት አስፈላጊ ይመስለኛል።

ሁለተኛ ይህ ሂደት ገና ጅማሮ ነው፣ ከእስር የመፈታቱ ሂደት በነዚህ ጥቂት ዜጎች ተጀምሯል፣ ቀስ በቀ ስ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ የሚፈቱበትና እርቁ እየሰፋ ሄዶ ዴሞክራሲና የተረጋጋ ህብረተሰብ ለሚመጣበት ሁኔታ በሩ ተከፍቷል ማለት አይቻልም። በዚህ በተጀመረው ሂደት ይበልጥ እርቅ፣ ይበልጥ ዴሞክራሲ፣ ይበልጥ ሰላም የሚ ገነባበት ሁኔታ ቢኖር ኖሮ ለዘመናት በግፍ አገዛዝ ጀርባው የተላጠ ህዝባችን "ነገ እይንህ ይበራልሃል ሲባል የዛሬን እን ዴት አድሬ" እንዳለው አይነ ስውር አጉል የሚቸኮልበት ምክንያት አይኖርም ነበር። ነገር ግን በዚህ ከፅንሱ የተኮላሸ የሽምግልና ሂደት ላይ የሚገነባ ምንም ነገር የለም። አካሄዱ የሃቀኛ ብሄራዊ እርቅ እድል የሚዳብርበት ሳይሆን የኮሰሰ በትና ጥርቅም ተብሎ የሚዘጋበት ሁኔታ ውስጥ እንደከተተን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምን?

መሳሪያ ስለጨበጡ ብቻ ያውም እነ በረከት ስምኦንን የመሰሉ ሰዎች እድሜውን ሙሉ ለህግ የበላይነት፣ ለፍትህ፣ ለሰላም፣ ለሃገር፣ ለወገን ሳያሰልስ የታገለ አባታችንን፣ አስተማሪያችንንና የሃገር አዛውንት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምን በእውኑ ቀርቶ በህልሙም የማያየውን "በፀረ ህገ መንግስት ዘዴ የመንግስት ለውጥ ለማምጣት" የሚ ል "የእምነት ቃል" እንዲሰጥ አድርገውታል። በዚህም "ወንጀል" አሱን የመሰለ ዜጋ እነ አቶ መለስ ዜናዊን "ይቅርታ " እንዲጠይቅ አስገድደውታል። በዚህ ሁሉ ላይ ሰሞኑን እነ በረከት ስምኦን በይፋ "የቅንጅት መሪዎች ተንበርክከው ይቅርታ እንዲጠይቁን አርገናቸዋል" እያሉ በግፍ ላይ እብሪት "ሲመርቁልን" ታዝበናል። ባጭሩ ለመናገር የተያዘው የ እርቅ ሂደት አይደለም። ይህ እርቅ ተብየ ነገር በህብረተሰባችን ውስጥ የባሰ ጥላቻ እንዲሰፍንና ህዝባችንም በህግ፣ በ ሰላማዊ ትግል፣ በፍትህ፣ በብሄራዊ እርቅ፣ በሽምግልናም ሃሳብ ተስፋ እንዲቆርጥ አድርጎት እልህና ጥላቻ ለተደባለቀ በት አስከፊ ትርምስና ትግል የሚገፋፋ አካሄድ ነው።

## ለ/ የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደትም "በጎ ጅማሮ" እንዳንባል

የጋዜጠኞች ከግፍ እስር መፈታት በቅድመ ግንቦት የነበረውን የፕሬስ ነፃነት መልሶ አላጎናፀፈንም። በነ ዚህ ወገኖቻችን መፈታት በቅድመ ግንቦት የነበረው የድርጅት ነፃነትና አንድ ድርጅት ለቆመለት ህዝባዊና ዴሞክራሲ ያዊ አላማ ዋና ባለጉዳይ የሆነውን ህዝብ ቀስቅሶና አደራጅቶ በህጋዊና በህገ መንግስታዊ መንገድ አንቀሳቅሶ ታግሎ ማ ታገል የሚችልበት ሁኔታ ተመልሶ አልመጣም። ደግመን ደጋግመን እንዳልነው ዛሬ በሃገራችን የተያዘው ትግል በአንድ በኩል በሚገባ የተዋቀረ፣ ገንዘቡ፣ ፖሊሱ፣ ሰራዊቱ፣ የመረጃ መረቡ፣ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፉ ያለው ፀረ ህዝብና አና ሳ ሃይል በሌላ በኩል ደግሞ በዴሞክራሲያዊነቱና በህዝባዊነቱ የማያወላዳ የበላይነት ቢኖረውም የፀረ ህዝቡ ወገን ድር ጅትም፣ ገንዘብም፣ አቅምም የሌለው የአገር ወዳዶች ሰፈር ነው። ይህ ግንባር ቀደም የሆነ ህዝባዊ ሃይል እሱም "አና ሳነቱንና" ከፀረ ህዝቦቹ አንፃር ያለበትን ድክመት "ማካካስ" የሚችለውና የፖለቲካ የበላይነት ይዞ ትርጉም ያለው የለ

ውጥ ሃይል የሚሆነው የኢህአዴግ መሪዎች በፀረ ህዝብ ፖለቲካቸው የተነሳ በምንም አይነት ከጎናቸው ሊያሰልፏቸው የማይችሏቸውን ሚልዮኖች ማንቀሳቀስ ሲችል ብቻ ነው።

ይህንን ጠንቅቀው የሚያውቁት ፀረ ህዝቦች ሌት ተቀን የሚያልሙት የኛ የሃገር ወዳዶችና የዴሞክራቶች ትግል ከነዚህ ሚልዮኖች ጋር ሳይገጥም በአየር ላይ የተንሳፈፈ የጥቂቶች "ግርግር" እንዲሆንላቸው ነው። እነዚህ ወገኖቻችን ላለፈው "ይቅርታ" መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም ህገ መንግስት "አክብረንና አስከብረን" እንንታገላለን የሚል ወረቀት እንዲፈርሙ ተገደዋል። ትላንትም ሆነ ዛሬም ነገም ትግላችን ህጋዊ ትግል እንደመሆኑ መጠን ቸግሩ "ህገ መንግስቱን እናከብራለን እናስከብራለን" ማለታቸው አይደለም። በዚህ በኩል ያለው ችግር ከኛ ሳይሆን ከኢህአዴግ መሪዎች ከራሳቸው ህገ ወጥነት የሚፈልቅ ችግር ነው። ያለው ችግር የዳኝነት ነፃነት በሌለበት፣ የህግ የበላይነት ደብዛው በጠፋበት፣ እነ አቶ መለስ እዛው በዛው "ዳኛም ቀማኛም" በሆኑበት ህገ መንግስታዊ ስርአት ተቃዋሚ ሃይሎች ህገ መንግስቱ በሚያውቅላቸው የድርጅት ነፃነት ተጠቅመው በግንቦት ማግስት እንደተሞከረው ህዝባዊ ስብሰባ፣ ሰላማዊ ሰልፍ፣ የስራ ማቆም አድማ ወዘተ ካሉ ይህ ሁሉ "ህገ መንግስቱ በማይፈቅደው መንገድ መንግስት ለመገልበጥ" የሚደረግ ወንጀል ተብሎ የመፈረጁ ችግር ነው።

ታዲያ በዚህ መልክ እነዚህ ወገኖቻችን ህዝባዊውን ተጋድሎ መልሰው ከማንቀሳቀስ አንፃር "እጅ ተወርች" ታስረው በተፈቱበት ሁኔታ ቀጣዩ ትግል እንዴት ይሆናል? የሚለው ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለዚህ ጥያቄ ቀላል መልስ አለኝ ብየ አልመፃደቅም። የዴሞክራቱና አገር ወዳዱ ሰፈር በጋራና በጥሞና ገና የሚወያይበት ጉዳይ ነው። ዋናው ቁም ነገር ግን እዚህ ላይ አይደለም። ዋናው ቁም ነገር ህዝብን ይዞ መታገል በወንጀልነት በመፈረጁ ሁላችንም የገባንበትን አጣብቂኝ አሳሳቢነት መገንዘብና ቀጣዩን የትግል ስትራቴጂ ለመንደፍ ከዚህ መራራ ሃቅ መነሳት እንደሚያስፈልግ መቀበሉ ላይ ይመስለኛል። ቀላልና አጭር ምሳሌ።

እነዚህ ወገኖቻችን እንዲፈቱ በውጭም በውስጥም ከፍተኛ ተጋድሎ ተካሂዷል። በተለይ በሃገር ውስጥ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በደሴ፣ በጎንደር፣ በጅማ፣ በአዋሳ...... በያለበት የህይወት መስዋእትነት ድረስ የተከፈለበት መራራ ትግል ተካሂዷል። የቅንጅት መሪዎች በተፈቱ ማግስት ባወጡት መግለጫ ይህንን ሃቅ በመገንዘብ ለታጋዩ ህዝብ ምስጋና አቅርበዋል። ከዚህ አልፎ በመሄድ "መሪዎቻችን ይፈቱ" እያሉ የተሰው ወጣቶችንና ሌሎች ዜጎችን ለማክበርና ለማሰብ፣ እንዲሁም የፀረ ህዝቦቹን አፈና ከኛ ከዲያስፖራው ኢትዮጵያውያን ይልቅ ገፈቱን የቀመሰውን ህዝባችንን ለማመስገን ከዚያም አልፎ የትግሉ ዋና ባለቤት ከሆነው ህዝብ ጋር ለመምከር በሃገራችን የተለያዩ ክፍሎች እየተዘዋወሩ ህዝባዊ ስብሰባዎች ማድረግ አስፈላጊ እንደነበረ ማንም የሚስተው አይመስለኝም። ሆኖም ሰሞኑን እንደምንታዘበው ከአዲስ አበባ፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ አዋሳ፣ ድሬዳዋ ወዘተ ይልቅ እንዲህ አይነቶቹን ስብሰባዎች በዋሽንግተንና፣ ለንደን፣ ብሩክሴልና በርሊን ወዘተ ለማድረግ እቅድ እየተያዘ ነው።

እንዲህ አይነቱ የቅደም ተከተል ማምታታት ከነዚህ በፖለቲካ የበሰሉ ታጋይ ወገኖቻችን በኩል ከተራ ዝንጋታ የመጣ አይመስለኝም። ዛሬ በሃገራችን ባለው የዴሞክራሲ ሁኔታ በቅድመ ግንቦቱ ወቅትም ሆነ በግንቦት ማግስት የነበረው የመደራጀት ነፃነት የማይታሰብ ነው። በመሆኑም ያኔ "ውዳሴ ለዴሞክራሲ" ተብሎ እንደተጠራው የሚያዝያ 30ው አይነት ሰልፍ የመጥራትም ሆነ ያኔ "ከእንግዲህ እንዴት እንገዛ?" የሚለውን ጥያቄ ከህዝብ መክሮ ለመመለስ በያለበት ህዝባዊ ስብሰባዎች ጠርቶ መምከር የሚቻል አይደለም። የቅንጅት መሪዎች ይህንን ምርጫ ያደረጉት ከእንግዲህ ምናልባት "ቀጣዩ ምርጫ" ሲቃረብ እንጂ ዛሬ ህዝብን ለስራ ማቆም አድማና ለሰላማዊ ሰልፍ ቀርቶ ለአዳራሽ ስብሰባ መጥራት እንኳን "የማይፈቅድ" እንደሆነ በመገንዘባቸው ይመስለኛል።

ያለንበት አጣብቂኝ ምንም አጓጉል ህልም (ኢሉዥን) የሚፈቅድ አይደለም። ህዝባችንን ይዘን እንዳንታገል ህገ ወጦቹ የኢህአዴግ መሪዎች እንዳሻቸውና እንዳመቻቸው የሚተረጉሟቸው ህግጋት እጅ ተወርች አስረውናል። ህዝባችንን ይዘን ካልታገልን ደግሞ ለዚች ሰማእት አገራችን ሰላም፣ ነፃነት፣ አንድነትና ዴሞክራሲ የሚሉ ነገር ጨርሶ የሚታሰብ አይደለም። ለሃገር፣ ለወገን፣ ለዴሞክራሲና ለሰላም ቆመናል ካልን የምንነድፈው ስትራቴጂ ሁሉ ከዚህ ሃቅ ተነስቶ ይህንን ያለንበትን አዙሪት የሆነ ቦታ ለመስበር የሚጥር ስትራቴጂ መሆን ይኖርበታል።

## 3ኛ. ከእንግዲህስ?

የግንቦት ድሎች ቅልበሳ ዋና ገፅታ ባለፉት 15 አመታት ቀስ በቀስ ዜጎች እየሞቱ፣ እየታሰሩ፣ እየተሰደዱ የገነቧቸውንና የኢህአዴግ መሪዎችን ለሽንፈት የዳረጓቸውን ውሱን የነበሩትን የዴሞክራሲ ተቋማትና የበጎ አስተሳሰብ ግኝቶች እንዳልነበሩ አድርጎ ለማውደም የሚደረግ ሙከራ መሆኑ ነው። እርግጥ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር የተሟላ ዴሞክራሲ ኖሮ አያውቅም። ነገር ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ በሌለበት ሁኔታ እንኳን በቅድመ ግንቦት በነበረችው የዴሞክራሲ የፍንጭ ፍንጭ ተጠቅሞ በፀረ ህዝቦች ላይ የማያወላዳ ድል ለመጎናፀፍ በቅቷል። የኢህአዴግ መሪዎች ከዚህ "የበኩላቸውን" ትምህርት ቀስመዋል። ገና በእንጭጭ የነበረው የዴሞክራሲ ሂደት ምን ያህል ኪሳራ እንዳደረሰባቸው ተገንዝበዋልና ከእንግዲህ እነዚህ ጥቂት ቀልባሾች በህዝብ ትግል ለህዝብ ፈቃድ ለመገዛት ከመገደዳቸው በፊት "ከባድ ከባድ" የሆኑት ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ቀርቶ በቅድመ ግንቦቱ ወቅት የነበሩት ፍንጮች እንኳን ተመልሰው እውን እንዲሆኑ አይፈቅዱም።

ከዚህ የኢህአዴግ መሪዎች አካሄድ የኛም ዴሞክራቶችና የሃገር ወዳዶች ጎራ የበኩሉን ትምህርት መቅሰም ከቻልን ስለሚጠብቀን አስቸጋሪ ትግል ግልፅ እይታ ይኖረናል። የቅልበሳውን አሳሳቢነት ሳናጣጥል፣ ስለ ቀልባሾቹ የአላማ ጥራትና ቁርጠኝነት በምንም ሳንዘናጋ የግንቦትን ድሎች ለማስመለስና እነሱን ተንከባክቦ በነሱ ላይ ለመገንባት የሚለውን ህዝባዊ አጀንዳ አንግበን ለዚህ ተግባራዊነት ደግሞ የህዝባዊ ትግልና የህዝባዊ አመራርን አስፈላጊነት መቀበል እንዳለብን እንገነዘባለን።

የግንቦት ድሎችን ያነገበ "ህዝባዊ አጀንዳ" ስንል የኢህአዴግ መሪዎች አፀፋ ምንድን ነው? የአካሄዳቸው ዋና ገፅታ በአስራ አምስት አመት አገዛዛቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በማያወላዳ ሁኔታ እነሱን ወደ ተከላካይነት የህዝብ ወገኖችን ደግሞ ወደ አጥቂነት ያሸጋገራቸውን የግንቦትን ምእራፍ ከትግል አጀንዳችን እንድናወጣላቸው ነው። ከዚህ ይልቅ ምኞታቸው የፖለቲካም ሆነ የዲፕሎማሲ የበላይነት አስይዞን የነበረውን የግንቦትን ታሪካዊ ምእራፍ ዘግተን በቅድመ ግንቦቱ ወቅት ሲደረግ እንደነበረው እነሱ ከወዲሁ አረጋግጠናል ብለው በሚመፃደቁባቸው የህግ የበላይነት፣ የዳኝነት ነፃነት፣ ተጠያቂነት፣ የፕሬስ ነፃነት፣ ነፃ ምርጫ... ወዘተ እያልን የነዚህ እሴቶች ሁሉ መቋጠሪያ የሆነውን የግንቦትን ጉዳይ ወደ ጎን የተወ "የአህያ ውድቂያ" ሊባል በሚችል የትግል ጎዳና እንድንኳትንላቸው ነው። በዚህ ደግሞ ብቻቸውን አይደሉም። በተቃዋሚው ጎራ ስለህዝባዊው አጀንዳችን ሲነሳ "ግንቦት ከእንግዲህ ታሪክ ነው" በሚል ክርክርና "ዴሞክራሲ ሂደት ስለሆነ..." በሚል ከነ አቶ መለስና ከባእዳን በቀለቡት ፈሊጥ የኢህአዴግ መሪዎች የማይዘጉትን የግንቦት ቅልበሳ ፋይል ዘግተን በሰከነ ትግል "ለቀጣዩ እንከን የለሽ ምርጫ" እንዘጋጅ እያሉ በሰዶ ማሳደድ አጉል ስትራቴጂ እንድንሰማራ የሚመክሩ ወገኖች አሉ።

ሁለተኛ ደግሞ ይህንን ህዝባዊ አጀንዳ ካነገብን ግንቦት የሚልዮኖች ድል እንደመሆኑ መጠን በዚህ ትግል ለመግፋት "በህዝባዊ ትግል" ሚልዮኖችን አሰልፈን እንፋለማቸው የሚል ስትራቴጂ አለን። የኢህአዴግ መሪዎች በአንድ በኩል በአመፅና በህገ ወጥ አካሄድ ህገ መንግስቱ ብቻ ሳይሆን የኢህአዴግ መንግስት ራሱ የፈረማቸው የአፍሪካም ሆነ የአለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች በሚፈቅዱለት መሰረት ህዝባችን ሰላማዊ ሰልፍ፣ ስራ ማቆም አድማ፣ ህዝባዊ ስብሰባ በሚሉ ዘዴዎች እንዳይጠቀም እነዚህን ሁሉ "ህገ ወጥ" አድርገዋቸዋል። በተቃዋሚው ጎራም ለዚህ የኢህአዴግ ፀረ ህዝብ ስትራቴጂ ተንበርክከው ሚልዮኖችን የሚያሰልፍ ህዝባዊ ተጋድሎ በሃገሪቱ አለመረጋጋት ሊፈጥር የሚችል አጉል ፍጥጫ አድርገው በመቁጠር ከዚህ ይልቅ የሃገራችንን ችግሮች በሰለጠነ ሂደት፣ በድርድር፣ በብሄራዊ እርቅ መንፈስ፣ በሽምግልናና በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ጫና መፍታት እንችላለን እያሉ ትግላችንን ለማዝረክረክ የሚሰሩ ወገኖች እንዳሉ ግልፅ ነው።

ለህዝባዊ አጀንዳ ህዝባዊ ትግል ስንል ይህንን በተግባር ለመተርጎም የሚያስችል ከፖለቲካ ድርጅቶች እጅግ የሰፋ ለዘርፈ ብዙውና ሁሉን አቀፉ የነፃነት ተጋድሎ ብቁ የሆነ እሱም "ሁሉን አቀፍ" የሆነ የጋራ አመራር እንላለን። የኢህአዴግ መሪዎች ይህን የጋራ ተጋድሎ ለማዝረክረክና ለማዳከም የዴሞክራቶችን ጎራ ሃላፊነት በሚሰማቸው "ተቃዋሚዎችና" በአክራሪዎች፣ በሃገር ውስጥ ባሉና በዲያስፖራው ወዘተ.... እያሉ ለመከፋፈል ሌት ተቀን ሲሰሩ ቆይ

ተዋል። እኛ ትግሉ በጠቅላላው በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ዴሞክራቶች ሁሉ የጋራ ትግል ነው ስንል በተቃዋሚው ጎራ ይህንን መሰረታዊ እውነታ በመካድ የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ ብቻ አድርገው የሚያዩ፣ ይህ አልበቃ ብሎ ደግሞ ከ ፖለቲካ ድርጅቶች እንኳን "የኛ ብቻ ነው" በሚል አጉል አቅጣጫ የተሰማሩ ወገኖች እንዳሉ ስንታዘብ ቆይተናል። የ ውጩን ትግል ከውስጡ ለመነጠል የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ "የዲያስፖራ አክራሪዎች" የሚለውን ቀልበው ውጭ ያለ ው ሃይል ከነሱ ልዩ አቋም ባንፀባረቀ ቁጥር "የሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ያልገባቸው ጥቂቶች" እያሉ ለማንኳሰስ የሚሞ ክሩ ሃይሎች አሉ። ከነዚህ መሃል አንዳንዶቹ ደግሞ ዲያስፖራው ከነሱ የሚስማማ አቋም ሲያንፀባርቅ እንኳን ተሳት ፎውን "በስንቅ አቀባይነት" ብቻ ለመወሰን ጥረት ሲያደርጉ ታዝበናል። የጋራ ትግልንና አመራርን በተመለከተ እነዚህ ወገኖች እርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ "እንደ አንድ ሰው" ሆኖ እንዲነሳ በተደጋጋሚ ጥሪ ያደርጋሉ። ነገር ግን ይህ ጥሪ ያቸው "እንደ አንድ ሰው ሆነህ ከኛ ጀርባ ተሰለፍ!" የሚል አጉል ቅስቀሳ እንደሆነ ለመረዳት እስካሁን ድረስ "የጋራ ትግል በጋራ ስትራቴጂ" እየተባለ ለዚህ ደግሞ አንድ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ለሚለው ጥሪ ጆሮ ዳባ ሲባል መቆየቱን መታ ዘብ ይበቃል።

ከዚህ ሁሉ አንፃር በነዚህ ወገኖቻችን መፈታት የተፈጠረው የፖለቲካ ሁኔታ ምን አዲስ ነገር ያመጣል? በአንድ በኩል በእኛና በሌላ በኩል ደግሞ በኢህአዴግ መሪዎችና በሰከኑ ተቃዋሚ ተብየዎች ባለው የአላማና የአካሄ ድ ምርጫ በኩል ምንም ለውጥ አይኖርም። ሆኖም እኛ ዴሞክራቶች በተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ተጠቅመን ነባር ስት ራቴጂያችንን ለማጠናከርና በሱ ላይ ለመገንባት ፅኑ ፍላጎት እንዳለን ሁሉ ፀረ ህዝቦቹም የቻሉትን ያህል በሁኔታው ነባ ርና ፀረ ህዝብ አላማቸውን ለማራመድ ሊጠቀሙበት እንደሚሞክሩ ለአንዲት አፍታም ቢሆን መዘንጋት አያስፈልግም። ፀረ ህዝቦቹ በዚህ ሁኔታ ተጠቅመው ትግላችንን ለማሽመድመድ ሁለት "ካርዶች" ለመጠቀም እንደሚሞክሩ ሳይታለ ም የተፈታ ጉዳይ ነው።

የመጀመሪያው ከዚህ "የተሳካ" የሽምግልና ሂደት "የተቀሰመ ትምህርት" ተብሎ የሚቀርበው ማወናበጃ ነው። የኢህአዴግ መሪዎች ከእንግዲህ ህዝብን ይዞ በህጋዊ መንገድ የመታገልን ነገር "በህገ ወጥነት" ፈርጀው በዚህ በኩል የሚደረግ ማንኛውንም ሙከራ በአመፅ እንደሚቋቋሙት ግልፅ አድርገዋል። ታማኝ ተቃዋሚዎች፣ አንዳንዶቹ ሽማግሎችና ባእዳን ለዚህ የኢህአዴግ መሪዎች የውንብድና ሂደት የፖለቲካና ዲፕሎማቲክ ድጋፍ ለመስጠት ሲሞክ ሩ እናያለን። ከዚህ "የተሳካ" የሽምግልና ሂደት "የተቀሰመው ትምህርት" በሚል ከእንግዲህ የህዝብ ተሳትፎ ሳያስፈ ልግ የሃገራችን ችግሮች በድርድር፣ በብሄራዊ እርቅ መንፈስ፣ በሃገር ሽማግሎች ጥረት፣ በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ጫና ሊፈቱ እንደሚችሉ "ተረጋግጧል" እየተባልን ነው።

ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ ጥረታቸውን ለመቀጠልና ከቃሊቲ አልፎ በጠቅላላ በሃገሪቱ ያሉ የፖለቲካ እ ስረኞች እንዲፈቱ በመላ በሃገሪቱ "የሽምግልና ሰንሰለቶች" የሚሉ ነገር ለመዘርጋት እቅድ እንዳላቸው ገልፀዋል። ግን ደግሞ በዚህ አላቆሙም። በአንድ ቃለ ምልልስ ላይ ከዚህ አልፈው ተርፈው ከሳቸው "ሰንሰለት" ውጭ በሃገርም ሆነ በውጭ የሚደረግ ማንኛውም ህዝባዊ ትግል ፍሬ መስጠት የጀመረውን ጥረታቸውን "እንደሚያወሳስብባቸው" አስጠን ቅቀዋል። ለዚህም አንደ "ተጨባጭ" ምሳሌ ይጠቅሳሉ። እነዚህን ወገኖቻችንን ለማስፈታት ከነ አቶ መለስ ጋር ላይ ታች በሚሉበት ወቅት "መሪዎቻችንን ይፈቱ" እየተባለ በውጭ አገሮች የተካሄደው የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትግል የነ ዚህን ወገኖች መፈታት ጉዳይ "ለሰባት ወራት ያህል" እንዳራዘመባቸው ተናግረዋል። ጥሪው ግልፅ ነው። የሃገራችንን ሆነ የነስለሺ ሙለታን ጉዳይ ፍቱንነቱን ላሳየው የሽምግልናና የድርድር ሂደት ለኛ "ለሽማግሎቹ ተውት!" የሚል አዘና ጊ ጥሪ ነው። ከዚሁ አይነት "የሰከነ አካሄድ" ፍቱንነት ቴዎሪ በመነሳት የቅንጅት መሪዎች በተፈቱ ማግስት አቶ ልደ ቱ አያሌው "ይኸው የኛ መስመር ትክክለኛነት ተረጋግጧል፣ የቅንጅት መሪዎች ዞሮ ዞሮ የኛን ጎዳና መያዛቸው ላይቀ ር እኛን "ከሃዲዎች" ብለው ወንጅለውናል" በሚል አነጋገር ምሬቱን ከገለፀ በኋላ እሱም የአቅሙን እንደነ አቶ መለስ "ይቅርታ ልጠየቅ" ብሎ ሲግደረደር ተደምጧል።

እንዲህ አይነቱ አጉል አካሄድ እስካሁን በነዶ/ር በየነ ተሞክሮ እኛም ህዝባችንም "አድርሰናል" እያልን ስንቃወመው የቆየነው ነገር እንደሆነ የኢህአዴግ መሪዎች ጠንቅቀው ያውቃሉ። በውስጥም በውጭም የዴሞክራቶችን ጎራ መከፋፈልና ማዳከም ከሚለው የነአቶ መለስ ህልም አንፃር እነ ዶ/ር በየነ "ባትሪ ያለቀባቸው" ተቃዋሚዎች እን

ደሆኑ ፀሃይ የሞቀው ሃቅ ሆኖባቸዋል። በዚህ የተደናገጡት የኢህአዴግ መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው የህዝቡን ትግል መስመር ለማሳት የሚጠቀሙበት ሁለተኛ ካርድ አለ።

ሁለተኛው ካርዳቸው በተፈቱት ወገኖቻችን በተከፈለው መስዋእትነት በመነገድ የተዳከመው የታማኝ ተቃዋሚዎች ጎራ "አዲስ እስትንፋስ" እንዲያገኝ መሞከር ነው። እነዚህ ወገኖቻቻን በከፈሉት የማይናቅና ክቡር መስዋእትነት በህብረተሰባችን ከነበየነ/ልደቱ በእጥፍ ድርብ የሚበልጥ ተደማጭነት አላቸው። በዚህም የተነሳ የኢህአዴግ መሪዎች የሌት ተቀን ህልም ከተፈቱት መሃል ቢያንስ የተወሰኑ ክፍሎች የምቹ ተቃዋሚዎቹን አካሄድ ቀልበው እነሱም የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት፣ ድርድር፣ አለም አቀፍ ኮሙኒቲ፣ ቀጣይ ምርጫ ......በሚሉ የህዝብ ትግል አሳች መፈክሮች ዙሪያ እንዲቆሙላቸው ነው። ስሌታቸው እነዚህ ወገኖቻችን ሰማእታት ናቸውና የነሱን አካሄድ መቃወም የእነ ዶ/ር በየነን አካሄድ እንደ መቃወም ቀላል አይሆንም የሚል የተሳሳተ ስሌት እንደሆነ ግልፅ ነው። በኛ በኩል መስጠት የሚገባን መልስ ደግሞ የዚያኑ ያህል ግልፅ መሆን ይኖርበታል። በሁኔታው ለመነገድ መሞከር ሳይሆን ባለው ላይ መገንባት የሚል ስትራቴጂ አለን። በመሆኑም በተከፈለው መስዋእትነት ትግሉን ይበልጥ መስመር ለማስያዝ እንጠቀም በታለን እንጂ ማንም ይሁን ማን የህዝባችንን ትግል ለማዝረክረክ እንዲነግድበት አንፈቅድም። ለምን? እንዴትስ እንገነባበት?

መጀመሪያ ነገር የመስዋእትነትን ነገር አንስቶ በዚህ ለመነገድ ከተሞከረ እኛም ስለ መስዋእትነት የምንለው ብዙ ብዙ ይኖረናል። የመስዋእትነት ነገር ከተነሳ አሁንም ቢሆን እነ ስለሺ ሙለታ በእስር እየማቀቁ በልጅ፣ በሚስት፣ በወላጅ በዘመድ አዝማድ መከራ፣ ሰቆቃና የኑሮ መመሰቃቀል አይከፍሉ መስዋእትነት በመክፈል ላይ እንደሆኑ ስ አፍታም ቢሆን እንደማንዘነጋ እናስታውሳቸዋለን። የመስዋእትነት ነገር ከተነሳ እነዚህን መስመሮች በምፅፍበት ወቅት ይህ የጨካኞች አገዛዝ ለሚለንየም ሽርጉድ በሚልዮን እየቆጠረ ገንዘብ እያባከነ ባለበት ወቅት የወጣ አንድ የዩኒሴፍ ሪፖርት በሚቀጥለው አንድ አመት በሃገራችን በቀላሉ መከላከል ይቻል በነበረ በሽታ 344ሽ ህፃናት ያልቃሉ ብሎ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ጠቅሰን በዚህም የተነሳ በኢትዮጵያ እናቶች የእንባ ጎርፍ የሚከፈለው ከባድ መስዋእትነት እንደ ሌለ መቆጠር አይኖርበትም እንላቸዋለን። የመስዋእትነት ነገር ከተነሳ ከድምፃቸው ጋር የፈቀዱትን አማራጭ ተዘርፈው በግፈኛና ለጥቂቶች በተበጁ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ሳቢያ ከቀን ቀን የእለት ጉርስ ችግር፣ ውርደትና እርዛት ላይ የሚገኙ ሚልዮኖችም መስዋእትነት መረሳት እንደማይኖርበት እንገልፅላቸዋለን።

ከዚህ በመነሳት እነዚህ ወገኖቻችን በከፈሉት መስዋእትነት እንገንባበት እንጂ ማንም አይነግድበት ሲባል ሌላ ምንም ትርጉም የለውም። አሁን በአይናችን ስር እየተከፈለ ያለውን የነስለሺ ሙለታን የሰማእትነትና የሰቆቃ ዘመን ሊያራዝም የሚችል ማንኛውንም አካሄድ እኛ የህዝብ ወገኖች ያለ አንዳች ማመንታትና ይሉኝታ በአንድ ድምፅና በጋራ በሰማእት ህዝባችን ስም ልንታገለው ይገባል ማለት ነው። ይህም ማለት የቅንጂት መሪዎች በከፈሉት መስዋእትነት ባገኙት ተገቢ ተደማጭነት ላይ በመገንባት በህዝቡ ወገን እንዲፀኑ፣ የህዝቡን አጀንዳ እንዲያነግቡ፣ ለዚህ አጀንዳ እውንነት ዋናው የትግሉ ባለቤት ፈረንጅም የሃገር ሽማግሌም ሳይሆን ህዝባችን መሆኑን ተቀብለው ታግለው እንዲያታግሉት፣ ለዚህ ደግሞ በውጭ ያለውን ቅንጅት ሲያባላ የቆየው እጅ እግር የሌለው ትርምስ እልባት አግኝቶ ድርጅቱ በአንድ እንዲቆም፣ ህዝባችንን በጋራ እንደ አንድ ሰው ለማሰለፍ ለሁሉን አቀፍ የጋራ ትግል ሁሉን አቀፍ የጋራ አመራር አስፈላጊነት ተገንዝበው ለዚህ አላማ እንዲሰለፉ መታገል ማለት ይሆናል።

እርግጥ ካለፈውም እንደተማርነው ሆነ አሁንም ጠብ ጠብ እያሉ ከምናያቸው ምልክቶች እንደምንረዳው (የወያኔ ተንኮልና ሴራ ታክሎበት) በፓርላማ መግባቱ ጉዳይ እንደታየው አሁንም በቀጣይ ስትራቴጂ ጉዳይ በአንድ በኩል ለወያኔ ስሌት በሚመቹና በሌላ በኩል ደግሞ በህዝባዊ አላማ በሚፀኑ መሃከል ልዩነቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ይህ ክፍፍል በቅንጅት በራሱም ውስጥ በዚህ መስዋእትነት ለመነገድ በሚፈልጉና በሱ ላይ ለሃገር ለወገን በጎ ነገር ለመገንባት በሚሹ መካከል እንደሚሆን ከወዲሁ መጠበቅ ይቻላል። በህዝባዊው ሰፈር የሚፀኑ የቅንጅት ታጋዮች በዚህ ህዝባዊ አቋማቸው የተነሳ "በአክራሪነት" ተፈርጀው አስቸጋሪ የሆነ ትግል ለማካሄድ ሊገደዱ የሚችሉበት ሁኔታም ሊፈጠር እንደሚችል ካለፈ ልምዳችን እናውቀዋለን። እንዲህ አይነቱ አይቀሬ ሊባል የሚችል ክፍፍል ወደ አደገኛ ውዥንብር ተሸጋግሮ የሰላሙና የዴሞክራሲው ትግል ብቻ ሳይሆን ጭራሹን ሃገራችን ባለቤት ያጣች ሃገር እንዳትሆን ከፈለ

ግን ብዙም አማራጮች የሉንም። ከውዥንብሩ አንፃር ጥራት እናመጣለን፣ ከወላዋዮች አንፃር ከዚህ ሰማእት ህዝባችን
ና ከሃገራችን ጎን ፀንተን እንቆማለን የምንል ሃይሎች መከተል የሚኖርብን ስትራቴጂ በሁለት ቃላት የሚጠቃለል ስት
ራቴጂ ነው። መጀመሪያ መሽጋሸግ። ከዚያ ደግሞ መሰባሰብ።

ይህ አይነቱ የመሽጋሸግና የመሰባሰብ ጥሪ በኢዴሃህ በተደጋጋሚ ሲሰነዘር ቆይቷል። መሽጋሸግ አለብን
ስንል ዛሬ ሃገራችን ካለችበትና በቀጣዩም ጊዜ ልትገባበት ከምትችለው ውጥንቅጡ የወጣ ሁኔታ አንፃር ''እዚህ ግቡ''
የማይባሉ ዘግናኝ ድርጅታዊ ስሌቶችን ወዲያ አሽቀንጥረን በመጣል ከአንድ መሰረታዊ እውነታ እንነሳ ማለት ነው። ዛ
ሬ ያለው ልዩነት በዚህና በዚያ ድርጅት መሃከል ሳይሆን በሁለት ሰፈሮች መሃከል ነው። በአንድ በኩል የፀረ ህዝቦቹና
በተቃዋሚነት ያሰለፏቸውና ሊያሰልፉ የሚሞክሯቸው ከየትኛውም ድርጅት ይሁን ከየትኛው እያፈነገጡ የሚገቡላቸ
ው የምቹ ተቃዋሚዎች ሰፈር አለ። በሌላ በኩል ደግሞ የድርጅት፣ የቡድንና የአንጃ ስሌት ሳያጥራቸው ለህዝባዊ አላ
ማ የቆሙ የፅኑ ዴሞክራቶችና የሃገር ወዳዶች ሰፈር አለ። ሁሉም ይህንን ተገንዝቦና በሁለቱ መሃከል ሌላ ሶስተኛ ጎራ
እንደሌለ አውቆ ሰልፉን ማሳመር ይኖርበታል። ይህም ሆኖ በዚህ መልክ መሽጋሸጉ ብቻ አይበቃም። በህዝባዊ ጎራ የ
ቆሙት ሃይሎች ከዚህ አልፈው መሰባሰብና ለመጭው አስቸጋሪ ትግል የጋራ ስትራቴጂ ነድፈው ሚልዮኖችን ያቀፈ የ
ጋራ ትግል ለመቀስቀስና፣ ለመምራትና ለማካሄድ ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል።

ይህ ስትራቴጂ እውን እንዲሆን ከተፈለገ ህብረታችን በተደጋጋሚ ያደረገው ''የሁሉን አቀፍ ጉባኤ'' ጥሪ
ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊም አጣዳፊም እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። በአንዳንድ አካባቢዎች ''ሁሉን
አቀፍ ጉባኤ'' ስንል ግራ በመጋባትም ይሁን ሆን ብሎ ግራ ለመጋባት '' ኢህአዴግ እያለ እንዲህ አይነቱ ጉባኤ ሃገር ው
ስጥ ሊደረግ አይችልም'' የሚል አነጋገር አለ። በዚህ ጉዳይ ከወዲሁ ግልፅ መሆን ያለበት የምናወራው ስለ ሁለት ጉባ
ኤዎች መሆኑ ነው። አንደኛውና የትግሉ ወሳኝ ምእራፍ የሚሆነው በህዝባዊ ተጋድሎ የኢህአዴግ መሪዎች ለህዝብ ፈ
ቃድ እንዲገዙ ከተገደዱ በኋላ በሃገራችን ምድር የሚሰየመው ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ሸንጎ ወይም ጉባ
ኤ እንደሆነ በህብረታችን በተደጋጋሚ ተገልጿል። ሁለተኛው ወደዚህ ወሳኝ ጉባኤ ለሚደረገው የጋራ ትግል አስተዋፅ
ኦ ለማድረግ በሁኔታው አስገዳጅነት በውጭ አገር የምንጠራውና የጋራ የትግል ስትራቴጂና መዋቅር ዘርግቶ ትግሉን ፈ
ር ለማስያዝ የሚያግዝ ጉባኤ ይሆናል።

እርግጥ የእንዲህ አይነቱን ጉባኤ ሃሳብ የዲያስፖራውን ሚና በስንቅ አቀባይነት ብቻ ለመወሰን የሚጥሩ
ወገኖች ሊያጣጥሉት ይችላሉ። ክርክራቸውም እጅ እጅ እስኪለን ሰምተነዋል። የኢህአዴግ መንግስት በውጭ የሚኖሩ
ትን ሚልዮኖች በሃገራቸው ጉዳይ ''ፖለቲካ እንዳይገቡ'' በፀረ-ዲያስፖራ ፕሮፓጋንዳ ከመሰማራት ዘልቆ በምርጫ የ
መሳተፍ መብታቸውን እንደነፈጋቸው እናውቃለን። እነዚህ ወገኖች ደግሞ ''ዋናው ትግል ሃገር ቤት ነው፣ ከውጭ ሊ
መራ አይችልም!'' በሚል ከብት ባልዋለበት ኩበት ለመልቀም በሚግደረደር ክርክር የዲያስፖራውን የፖለቲካ ተሳትፎ
ለመገደብ ይቃጣቸዋል። በውጭ ያለው ሃይል በጋራ ይቁም ሲባል ለጠቅላላው ትግል የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማድረግ
እንጂ የውስጡን ''እንዲመራ'' አይደለም። ይህ አስተዋፅኦ ደግሞ የሚያመረቃ የሚሆነው በውጭም ቢሆኑ ከወዲሁ በ
ትግል ላይ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ስብስቦች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የጋዜጠኞች ወዘተ ስብስቦች የምሁራ
ንና የታዋቂ አገር ወዳድ ተወካዮች ተገናኝተው ለጋራ ትግል፣ የጋራ ስትራቴጂና አታጋይ አካል ለመፍጠር ሲጥሩ እን
ደሆነ ለማንም ግልፅ ነው። የእንዲህ አይነቱ የጋራ ጉባኤና የጋራ ትግል ጉዳይ አስፈላጊነት ከፀሃይ ደርቶ የሚታይ በመ
ሆኑ ሃሳቡን ለመቃወም አንድ እዚህ ግባ የሚባል ምክንያት የሰጠ ዜጋ እስካሁን አላጋጠመኝም።

ለሚያስፈልገው ''መሰባሰብ'' እንዲህ አይነቱ ጉባኤ የግድ ''ተቃዋሚ ነኝ'' የሚለው ሁሉ እስኪሰባሰብ
መጠበቅ የለበትም። ጊዜ ለቀልባሾቹ እንጂ ለኛ እንደማይሰራና ትግላችን ከአደገኛ ዳተኝነትም ጋር መሆኑን መገንዘብ
ያስፈልጋል። በመሆኑም በሆነ ባልሆነ ነገር ሊያራዝሙ የሚሞክሩ ሃይሎችን ወደ ጎን ትቶ ፈቃደኛ ከሆኑ ወገኖች ጋር
ይህንን ጉባኤ ተግባራዊ ለማድረግ መስራት የግድ ይሆናል። ያልነው አካሄድ የህዝባዊ ሃይሎች ''የመሰባሰብ'' ሂደት ነ
ውና በህዝባችን ጎን የፀናን ወገኖች ቁጥራችን አነሰ የሚል ስጋት ሊኖረን አይገባም። እንሽጋሸግ እንሰባሰብ የምንለው የ
ሃገሩም፣ የትግሉም ባለቤት የሆኑትን ሚልዮኖችን በግልፅና ህዝባዊ አማራጭ ዙሪያ ታግሎ ለማታገል የሚደረገውን ጥ
ረት ለማገዝ ነው። ጥሪው እስካሁን ከተያያዝነው ''የከቦ ማዋከብ'' ትግል ተላቀን ሁሉም በአንድ አቅጣጫ የሚገፉበት

ን ሁኔታ እናመቻች የሚል ጥሪ ነው። ለዚህ እውነነት ደግሞ ያለው ችግር የጥራትና የቁርጠኝነት እንጂ ሳር ቅጠሉ ለ ሃገርና ለወገን ቆሞ ይህንን የግፍ አገዛዝ በሚቃወምባት ምድር የቁጥር ችግር እንደሌለብን ጠንቅቀን መረዳት ይኖርብና ል።

ነሃሴ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.